# <u>አሰፋ ጫቦ ተብየው እንደ አይሲስ ሕዝብን በጥይት የመቁላትና አገር የማጥፋት ባህሪ የተጠናወተው፣እጁና ታሪኩ በደም የተነከረ አረማዊ የደርግ ቀይ ሽብር ኮሚሳርና የወያኔ ደጋፊ ኮብላይ</u>

ከአስተዋይ በቀለ

ይህ አሰፋ ጫቦ ተብየው እንደለመደው ግንቦት 7 ውስጥ በአድርባይ ምስለኔነት ለመቀላወጥ ኢሳት ላይ ቀርቦ እንደተነጠረቀውና እንደተቀደደው ዓይነት ሰው አይደለም።

አሰፋ ጫቦ አፍ ከዳን የማያውቅ፣ ምላሱ ያልተገረዘ ተቅበዝባዥ ቧግዲ አፍ ቅድ ሞገደኛ ነው። አሰፋ ለገሙ ምድር እርግማን ሆኖ የተወለደ የእፉኝት ልጅ ሲሆን በጥፋቱ እየሰጋና በራሱ ላይ እየሸና የሚኖር በርጋጊ ባንዳ ነው።

ከመነሻው የተማሪን ንቅናቄ ለመኳንቱ ይሰልል የነበረ፣ የሲቪል አቤሽን ሠራተኞች በአድማ ከሥራው ያባረሩት፣ ልጅ እንዳልካቸው መኰነንና ሻለቃ አጥናፉ ላይ ተለጥፎ በአጉል ምክር በማንሿከክና በማሳሳት ለሞት ያበቃቸው፣ ከደርግ ጋር በመወገን ቀድሞ _ ተሽቀዳድሞ ታጥቆ የቀይ ሽብር ኮሚሳር በመሆን በኢትዮጵያ ሕዝብና በወጣቱ የለውጥ ተስፋ ላይ በጥይት የዘመተ፣ ኃላም በጠባብ ዘረኝነት ለወያኔ አድሮ ኤርትራን ያስገነጠለ፣ አገር በክልል ያስከፈለና ሕዝብን አነጣጥሎ ለዛሬው ግፍና በደል የዳረገ ባጠቃላይ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትንና ሰንደቅ ዓላማችንን የጎዳና ትሪዝን የፈፀመ ባንዳ ነው።

**ልብ በል ወገን !** በገብረ ደርግ _ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብና ወጣት ልጆቹን የጎዳ፣ ሕዝብ አነጣጥሎ ያተራመሰና ያለያዩ፣አገር ያስፈረሰና ብሔራዊ ጥቅማችንን የጎዳ ሁሉ መጋለጣቸው፣ መያዛቸውና ለሕዝብ ፍርድ መቅረባቸው የማይቀር ነው።

አሰፋ ጫቦ ያረጀና ያፈጀ ክርታስ ቢመስልም ከሞት ወዲህ ሞዶ ሕዝባዊ ቅጣት፤ ከሞት ወዲያ ማዶ ደግሞ የሲዖል ስቃይ ይጠብቀዋል። ታሳ ! የሚል ገሙ ውይም ሳሊለነ ቅድስት የሚል ቄስ አያድነውም።

**ፍርድና ቅጣት ለባንዶች ! ! !**

**ኢትዮጵያ ከዘላለም እስከ ዘላለም ትኖራለች ! ! !**